ባሕረ-ሐሳብ

መቅድም

በስመ አብ በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ቤተክርስቲያናችን ባህረ ጥበብ (የጥበብ ባሕር)) በመባል ትጠራለች ይህም የሚያስረዳው ሰፊ የሆነ ቢመረምሩት የማያልቅ ዕውቀት ባለቤት መሆኗን ነው ከዚህ ጥልቅና ጥበብ ከተሞሉ የዕወቀት ዘርፎች አንዱ የባሕረ ሀሳብ ትምህርት ነው።

የባሕረ ሀሳብ ትምህርት በኢትዮጲያ ውስጥ በመጽሐፍ ቤት እየተሰጠ ያለ ዕውቀት ነው።ይህንን ትምህርት አብዛኛው ምዕመን አውቀውት በየዓመቱ ያሉትን በዓላትና አጽዋማት በቀላሉ እያወጡ መጠቀም ሲኖርባቸው በጣት የሚቆጠሩ ሊቃውንት አባቶች ካልሆኑ በቀር በአግባቡ የሚያውቀው የለም ነገር ግን ምዕመናን እንዲያውቁት እንዲማሩት ይመከራል በተለይም ውጣቱ ትውልድ ሊያውቅና ሊረዳ ያስፈልጋል።

ሰዎች ሁልግዜ በተደላደለ ቦታ ላይ አንቀመጥም አጋጣሚ ሆኖ ካህናት በማይገኙበት ቦታ ልንኖር እንችላለን እንዲሁም ዓረማውያን የሚበዙበት ዘመን ሊመጣ ይችላል ወይም ሃሳውያን የሚበዙበት ሀገር ውስጥ የሚኖርበት ጊዜ ስለሚኖር ማወቅ የውዴታ ግዴታ ነው እንዲሁም የባህር ሃሳብ ትምህርት በጣም በጥበባዊ መንገድ የተዘጋጀ አዕምሮ የሚያዳብርና የሚያስደስት ቤተ ክርስቲያንም ሀገርንም የሚያኮራ ጥበብ ነው ስለዚህም ይህንን በሂሳብ ስሌት (ቀመር) የታጀበ የቤተ ክርስቲያን ሀብት በደንብ ተምሮና አውቆ ለሌላው የማስተማር ኃላፊነት ይኖርብናል።

መፍትሔ-ቃላት

- **ባሕር** ፡- ዘመን
- **ሐሳብ** ፡- ቁጥር
- **ባሕረ-ሐሳብ** ፡- ቁጥር ያለው ዘመን
- **ዓመተ ዓለም** ፡- ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ ያለው ዘመን
- **ዓመተ ኩነኔ (ፍዳ)** ፡- ከፍጥረተ ዓለም እስከ ጌታችን መምጣት ድረስ ያለው ዘመን
- **ዓመተ ምሕረት** ፡- ከጌታችን ልደት ጀምሮ ያለው ዘመን
- **ቀመር** ፡- ቁጥር
- **ኬክሮስ** ፡- ብርሃናት የሚመለለሱበት ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋ የሃሳብ መስመር ፩(1) ዕለት= ፷(60) ኬክሮስ
- **አቅማር** ፡- የቁጥር ስሌት ማስያ (ማግኛ)
- **ዓዕዋድ** ፡- ዞሮ የሚመጣ፤የሚመላለሱ
- **መዓልት** ፡- የብርሃን ጊዜ ፤ የጸሐይ ብርሃን የሚታይባቸው ሰዓታት
- **መባቻ** ፡- መጀመሪያ፤ መግቢያ
- **መጠነ- ራቢዒት** ፡- አንድ አራተኛ ዓመተ ዓለም በአራት ተገድፎ የሚመጣው ቁጥር
- **መጠነ - ሳቢዒት** ፡- አንድ ሰባተኛ የመስከረም መባቻ ቀን ማስገኛ
- **አበቅቴ** ፡- ተረፈ ዘመን
- **መጥቅዕ** ፡- ነጋሪት ደውል ከዕለት ተውሳክ ጋር ተደምሮ መባጃ ሐመር ያስገኛል
- **ወንበር** ፡- ገባር፤ተረፈ ንዑስ ቀመር፤
- **ሳኒታ** ፡- ማግስት
- **ሕጸጽ** ፡- ጉድለት
- **ተውሳክ** ፡- ጭማሪ ፤ ተጨማሪ፤ማስተካከያ ፤ምድብ
- **መባጃ ሐመር** ፡- የአጽዋማት እና በዓላት ማስገኛ
- **ኢይወርድ** ፡- አጽዋማት እና በዓላት የሚመላለሱበት የታችኛው (ዝቅተኛው) ቀመር
- **ኢየዐርግ** ፡- አጽዋማት እና በዓላት የሚመላለሱበት የላይኛው (ከፍተኛው) ቀመር
- **ሕርግራግ** ፡- የአጽዋማት እና በዓላት አወጣጥ ሥርዓት ማስፈሪያ ሠንጠረዥ
- **መግደፍ (ግደፍ)** ፡- ለአንድ ዐውድ ተካፍሎ ከሚገኘው ውጤት የሚተርፈው ቁጥር
- **መጫን (ጭኖ)** ፡- አባዝቶ ፤ማባዛት
- **አትቶ (ማተት)** ፡- ቀንስ(ቀንሶ) ፤መቀነስ
- **አንድ አድርጎ(ማድረግ)** ፡- መደመር ፤ደምር(ደምሮ)
- **አሥርቆት** ፡- የሌሊት እና መዓልት የሚያድሩበት ሥርዓት የሚያመለክት
- **በአተ ጾም** ፡- የጾም መግቢያ
- **አይጋረ ጸሐይ** ፡- የጸሐይ እግሮች
- **አውታረ ጸሐይ** ፡- የጸሐይ ጨረሮች

ምዕራፍ ፩

ባሕረ-ሐሳብ

፩.፩ .ባሕረ-ሐሳብ ምንድን ነው?

- ባሕረ-ሃሳብ ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን በዐረብኛ አቡሻህር በአማርኛ የዘመን አቆጣጠር ይባላል፡፡በሌላ አጠራርም መርሐ-ዕውር አንድም ቁጥር ያለወ ዘመን በመባል ይጠራል፡፡ አንድም ሃሳበ ባሕር ይላል ምነው ሰለምን ዘመንን ባሕር አለው ቢሉ
- ባህር ቢፈስ አያልቅም ባህረ ሐሳብም ዘመንም ምጽአተ ክርስቶስ እስኪያግደው ድረስ ሰውን እያሳለፈ ይኖራል፡፡

፩.፪. ባሕረ-ሐሳብ ማለት ምን ማለት ነው?

- **ባሕረ -ሃሳብ** ከሁለት ጥምር ቃላት የተገኘ ሲሆን ባሕር ና ሃሳብ የሚሉት ቃላት ናቸው፡፡
- **ባሕር** ፡- ማለት ዘመን ማለት ነው፡፡

\በመዳልው ደለወ ዓለመ ወበ መስፈርት ስፍራ **ለባሕር**- እንዲል እግዚአብሔር ባሕርን በመስፈሪያ ሰራሁት ማለት ነው፡፡ዘመናት በጣም ብዙ ቢሆኑም በባሕረ-ሃሳብ ስሌት ይሰፈራሉና፡፡በዚህ የተነሳ ባሕር ዘመን ተብሏል፡፡

ሃሳብ ፡- ማለት ደግሞ ቁጥር ማለት ነው

ሃሳብ የሚለው ቃል ሀሰበ ከሚለው ግስ የተገኘ ነው፡፡ትርጉሙም ቆጠረ ማለት ነው፡፡

\ብጽዓን እለተሀድገሎሙ ኀጢአቶሙ **ወእለኢሀሰበሎሙ** ኩሎ ጌጋዮሙ\ እንዲል ኀጢያቱ ያልተቆጠረበት ሰው ምስጉን ነው፡፡መዝ 31፡1

በአጠቃላይ ስንመለከተው ባሕረ ሃሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው፡፡

፩.፫. ባሕረ-ሐሳብ መማራችን ጥቅሙ

- የቤተክርስቲያን ጥበብ የተሞላበትን ትምህርት ለማወቅ
- ከሀገር ተሰዶ መሄድ ቢከሰት አልያም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብንገኝ ጾም አንገድፍም በዓል አንረሳም፡፡
- ያለፉትን አመታት ሆነ ወደፊት እስከ ምጽአት የሚመጡትን በዓላትና አጽዋማት የሚውሉበትን ቀን ማወቅ ያስችላል፡፡
- የጠፉብንን ዕለታት ለማወቅ ይረዳናል፡፡

፩.፬ .ባሕረ-ሐሳብን ለማን ተገለጠ (ማን ደረሰው)

- የቤተክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት ባሕረ--ሃሳብን ለማወቅ ከሐዋርያት ጀምሮ ብዙ አባቶች ተመኝተው ነበር፡፡ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ይህ ረቂቅና ምጡቅ ትምህርት ለማን ተገለጸ ቢሉ ለመንበረ እስክንድርያ ፲፪ተኛ ጳጳስ ለነበረው ለቅዱስ ዴሜጥሮስ ነው፡፡

፩.፬.፩. ቅዱስ ዴሜጥሮስ

ቅዱስ ዴሜጥሮስ ገበሬ የነበረ ምንም አይነት የቤተክርስቲያን ዕውቀትያልነበረው ሰው ነበር፡፡ የዴሜጥሮስ አባት እና አጎቱ /የአባቱ ወንድም/ በዘመነ ሰማዕታት በባዕድ ሐገር ከኢየሩሳሌም ተሰደው ይኖሩ ነበር፡፡የዴሜጥሮስ አባቱ ደማስቆ ወይም እንዲራኒቆ ስሲሆን አጎቱ ደግሞ አርማስቆስ ወይም አስተራኒቆስ ይባላል፡፡ሁለቱም በፋርስ ባቢሎን ለረጅም ዘመናት ሲኖሩ ከእነርሱ ቤተሰብ በስተቀር የማያምኑ አሕዛብ ነበሩ፡፡

አርማስቆስ ማለትም የዴሜጥሮስ አጎት ልዕልት ወይን የተባለች ሴት ውብ ልጅ ነበረችው ፡፡እርጅና እየተጫነው ሲታገለው ነግ እሞት ዛሬ እሞት አላውቀው የልጄ ነገር እንዴት ይሆናል እያለ ልቦናው ይረበሽ ነበር፡፡አንድ ቀን ለወንድሙ ለደማስቆ ልጄን ለአሕዛብ እንዳትድርብኝ ብሎ በእግዚአብሄር አስምሎት የተቆረጠለት ቀን ደርሶ ይሞታል፡፡

ደማስቆ ወንድሙ የሰጠውን አደራ ይዞ ለብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ ልዕልት ወይን ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ እንግዲህ ዘር ልትተካና ልታበዛ ያስፈልጋል እያለ ማሰብ ጀመረ፡፡በዚያው ጊዜ የደማስቆ ልጅ ዴሜጥሮስ ለአቅመ አዳም ደርሶ ነበርና ልጄን ለአሕዛብ ድሬ የሃይማኖት ህንጻ ከማፈርስ ከወንድሜ ልጅ ጋር ድሬ ሕንጻ ስጋን /የስጋ ዝንድናን/ባፈርስ ይሻላል ብሎአጋባቸው፡፡ አባቱ እንዳሰበለትም ዴሜጥሮስ የአጎቱን ልጅ ልዕልት ወይንን በሰርግ ያገባታል በሰርጋቸው ማታ በጫጉላ ቤት ተዘጋጅቶላቸው በቤቱ ደስታ ተድላ ሲደረግ ሁለቱ ሙሽሮች ግን በሀዘን ያለቅሱ ነበር፡፡ልዕል ወይን ስለምን አደረክ ብላ ብትጠይቀው / ከመ እፈጽም ፈቃደ አቡየ/ የአባቴን ፈቃድ እፈጽም ዘንድ አላት ከዚህ በኂለ ሁለቱ በአንድ በድንግልና ለመጽናት ተስማማሙ ያለሩካቤ ስጋ በድንግልና ሊኖሩ በሰው ዘንድ ግን እንደባልና ሚስት እየመሰሉ ኖሩ፡፡

ይህን ያደረጉበት ዋነኛ ምክንያት አባቱን ላለማሳዘን ነው፡፡ታዲያ ለምን አልተፋቱም ቢባል ባል የሌላትሴት ሁሉም ይመኛታልና ከአሕዛብ ጋር እንዳትጋባ ለመጠበቅ አብሯት ኖሯል፡፡በዚህ ሁኔታም ለ 48 ዓመታት በድንግልና ኖረዋል፡፡

የዴሜጥሮስ ስራው ግብርና ስለነበረ አንድ ቀን ወደ ማሳው በገባ ጊዜ ያለጊዜአቸው ያፈሩ ሶስት ዛላ እና አንድ የወይን ዘለላ በማግኘቱ በጣም ተገርሞ ከልዕልት ወይን ጋር ተመካክሮ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወሰደው፡፡በዚህ ወቅት የመንበረ እስክንድርያ11ኛ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ዮልያኖስ ከእድሜ ብዛት የተነሳ በማርጀቱ ከእርሱ ቀጥሎ የሚሾመውን ጳጳስ ማን እንደሚሆን በሱባዔ አይቶ ሕዝቡን በቤተ እግዚአብሔር ሰብስቦ ሊነግራቸው ሲል ቅዱስ ዴሜጥሮስ ከእርሻው ያየውን ምልክት ይዞ መጥቶ ለቅዱስ ዮልያኖስ ይሰጣል፡፡ጳጳሱም ቅብዓ ሜሮን ቀብቶ ሲመተ ጵጵስና ፈጽመውለታል፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ቅዱስ ዴሜጥሮስ አያውቅም ነበር ከጥቂት ቀናት በኋላ ቅዱስ ዮልያኖስ አረፈ፡፡ሕዝቡም ተነግሯቸው ስለነበረ መንበር ባዶውን አያድርም በአባታችን ቦታ ተቀመጥ አሉት፡፡ቅዱስ ዴሜጥሮስም እኔ በአንድ በኩል መሀይም ገበሬ ነኝ በሌላ በኩል ሕጋዊ ሚስት ያገባሁ ነኝ እንደምን በንጹህ በማርቆስ ወንበር እሾማለሁ ብሎ ቢቃወማቸው ግድ አሉትና ሾሙት፡፡ከዚህ በኋላ ቅዳሴና እና መጻሀፍተ ብሉይና ሐዲስ ተገለጸለት አስተምሯል፡፡

ቅዱሰ ዴሜጥሮስ በቅድስና እየበረታ ሲመጣ የሕዝቡ ኃጢያት እየታየው አንተ በቅተሀል ቁረብ አንተግን ገና ነህ እያል ይመልስ ነበር፡፡በዚህ የተነሳ ሕዝቡ እኛ ሾመነው በማርቆስ ወንበር ስናስቀምጠው አትቁረቡ ይለናል ብለው በሐሜት ወደቁ፡፡ቅዱስ ሚካኤል ተገልጦ ዝም ብልህ ሕዝቡ በሀሜት ተጎዳ በአንተና በልዕልት ወይን ያለውን ግለጽ ብሎ አዞታል፡፡

ቅዱሰ ዴሜጥሮስ ህዝቡ አንድ አንድ እንጨት ይዘው ይመጡ ዘንድ አዘዛቸው፡፡እንጨቱን አስደምሮ/አቃጥሎ/ ቅዳሴ ገባ ከቅዳሴ ወጥቶ በእሳት ውስጥ እየተመላለሰ አጥኗል ፡፡ልዕልት ወይን ከመቅዋመ እንስት /ከሴቶች መቋሚያ/ጠርቶ ልብስሽን ዘርጊ በማለት ልብሷ ላይ ፍሙን ዘግና ቢያስቀምጠው ከልብሷ ላይ አንዲት ሳይጠቁር ቀርቷል፡፡

ምዕመናንም የሚያደርገውን አይተው አባታችን ሆይ ይህንን ለምን አደረክ ቢሉት እኔ እከብርበት ብዬ ሳይሆን እናንት በሀሜት ኃጢያት እንዳትጎዱና ከእግዚአብሔር እንዳትጣሉ በማለት ነው፡፡

ይህ ፍም እሳት እንዳላቃጠልን ሁሉ እኔ እና እሷ ስንኖር በአዳማዊ ግብር/ በስጋዊ ተራክቦ/ አንተዋወቅም ሲላቸው - **ኃጢያታችንን ይቅር በለን-** ብለው ከእግሩ ተደፍተው ለምነውታል፡፡- እግዚአብሔር ኃጢያታችሁን ይቅር ይበላችሁ- ብሎ ናዝዞቸዋል፡፡ነዛዜም በዚህ ግዜ እንደተጀመረ አባቶቻችን ይናገራሉ፡፡

ቅዱስ ዴሜጥሮስ በጵጵስናው ወቅት ትልቅ ምኞት ነበረው በብሉይ ኪዳን ዘመን ወንጌላውያን አመቱን ለአራት ይከፍሉታል፡፡

<u>ለማቴዎስ</u> ፡- 3 ወር / 1 ጳጉሜ

<u>ለማርቆስ</u> ፡- 3 ወር / 1 ጳጉሜ

<u>ለሉቃስ</u> ፡- 3 ወር / 1 ጳጉሜ

<u>ለዮሐንስ</u> ፡- 3 ወር / 1 ጳጉሜ

- አንድ የቀረችው ጳጉሜ **ለማቴዎስ ከነግህ - ቀትር**
  ለማርቆስ ከቀትር - ሠርክ
  ለሉቃስ ከሠርክ - መንፈቀ ሌሊት
  ለዮሐንስ ከመንፈቀ ሌሊት - ነግህ ይሰጡታል፡፡
- ስድስተኛ ጳጉሜ በአራት አመት አንዴ ስትመጣ ለአራቱ መግቦት ወቅት ሊቃነ ከዋከብት ለናርኤልና ለብርክኤል ለምልኤልና ለሕልመልሜሌክ ለእያንዳንዳቸው ፲፭ (15) ኬክሮስ እያካፈሉ ይሰጡ ነበር፡፡
- 1 (፩) **ዕለት - ፷ (60) ኬክሮስ** ነው፡፡
  1 (፩) **ኬክሮስ - ፷ (60) ካልዒት**
  1 (፩) **ካልዒት - ፷ (60) ሳልሲት.......** እስከ ሳድሲት እያለ ይዘረዝረዋል፡፡

እነዚህ ለአንዱ አንድ አመት መስጠትና በአላትና አጽዋማት ጥንተ ዕለታቸው በመጠበቅ እንዲጓዝ ይሻ ነበር፡፡ እነዚህም ..

- **ጾመ ነነዌ ፣ ዐቢይ ጾም ፣ ጾመ ሐዋርያት ፡- ከሰኞ**
- **ጾመ ድኅነት ፣ ርክበ ካህናት ፡- ከ ረቡዕ**
- በዓለ **ዕርገት ፡- ከ ሐሙስ**
- በዓለ ስቅለት ፡- **ከአርብ**
- በዓለ ደብረ ዘይት በዓለ ሆሳዕና ፣ በዓለ ትንሳዔ ፣ በዓለ ጰራቅሊጦስ ፤- **ከ እሁድ**
  ፡- ባይወጡ በጥንተ ዕለታቸው ቢውሉ ባይለዋወጡ እያለ ይመኝ ነበር፡፡

ቅዱስ ሚካኤል ወደ እርሱ መጥቶ ነገር በምኞት ይገኛልን ሱባኤ ገብተህ እየው/አግኘው/ ብሎ አዞታል፡፡ከሌሊቱ ፳፫ (23) ግባ አበቅቴ ይሁንህ ከቀኑ ፯(7) ግባ መጥቅዕ ይሁንህ ብሎ ነግሮታል፡፡ሌሊቱን አብዝቶ ቀኑን ስለምን አሳጠረው ቢሉ ቀን የታመመ ሲጠየቅ የታሰረ ሲጎበኝ ወንጌል ሲያስተምር ስለሚውል ቀኑን አሳጥሮ ሌሊቱን አስረዝሞታል፡፡

አንድ ሱባኤ ሰባት ቀናት ነው፡፡ስለዚህም

- ሌሊት የገባው 23 x 7 =161 ይሆናል በሰላሳ ስንገድፈው /ስናካፍለው/ 5 ደርሶ 11 ይቀራል፡፡**11ን አበቅቴ** ብሎታል ፡፡
- የቀን የገባው 7 x 7 = 49 ይሆናል 30 ስንገድፈው 1ጊዜ ደርሶ 19 ይቀራል ፡፡ ***19 መጥቅዕ*** ብሎታል፡፡ከዚህ በኋላ ቅዱስ ዴሜጥሮስ ኢየዓርግ ና ኢየወርድ ተገልጾለት ባህረ ሃሳብ አስተምሯል፡፡
- **19 ወላዲ መጥቅዕ / ጥንተ መጥቅዕ /**
- **11 ደግሞ ወላዲ አበቅቴ /ጥንተ አበቅቴ/** ሆነዋል፡፡

፩.፬.፪. ባሕረ -ሐሳብን ማን ይማረው ?

- በመጀመሪያ ደረጃ ካህናት ሊማሩና ሊገነዘቡት ግዴታ አለባቸው ለምን ቢሉ ካህን በዓላትን አጽዋማትን አውጥቶ ለምዕመናን ማስተማር ግዴታ አለበትና፡፡
- ምዕመናንም እንዲያውቁት እንዲማሩት ይታዘዛል በተለይም የሀገር ተረካቢ የሆነው ወጣቱ ትውልድ ተምሮ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

፩.፬.፫. ቅዱስ ዴሜጥሮስ ለምን ባሕረ ሐሳብን ደረሰ

ሀ. ተምኔቱ ሐሳቡ ይፈጸምለት ዘንድ

ለ. ተራርቆ የነበረውን በዓላትና አጽዋማትን ለማቀራረብ

ሐ. በዓላት ጥንት ዕለታቸውን ጠብቀው ሳይፋለሱ እንዲቆዩ

ምዕራፍ ፪

፪.፩. ባሕረ- ሐሳብ /ዘመን አቆጣጠር/ ጥንትነቱ

የባሕር-ሐሳብ /የዘመን አቆጣጠር/ ጥንት የነበረ ነው፡፡ከየት ነው ቢሉ ከፍጥረት ዓለም ፣ ከፍጥረተ ጨረቃና ከዋክብት ነው፡፡

- **ጥንተ ዕለት** ፡- አለም የተፈጠረበት ዕለት እሑድ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት ዕለት ስለሆነ ነው፡፡እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታት በስድስት ቀናት ፳፪ቱን ፍጥረታት ፈጠረ፡፡ የእግዚአብሔር ህልውናም በዚህ ታውቋል፡፡እነዚህ የፈጠራቸው የእጁ ስራዎች ፍጥረታት ደግሞ ለባሕረ ሃሳብ ትምህርት ጥንት ሆነዋል፡፡እንደምን ቢሉ የጊዜን ርዝማኔ ከጸሀይና ከጨረቃ ዑደት የሚገኝ ስለሆነ ነው፡፡
- **ዕለተ ጠቢባን** ፡- አለም የተፈጠረበት ዕለት እሑድና ሰኞ(ሰኑይ) ስላሴ ጠቢባም ከዕለታት መርጠው አለምን ስለፈጠሩባቸው ዕለተ ጠቢባን ይባላሉ፡፡
- **ጥንተ ቀመር** ፡- ቀመር ቀመረ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ቆጠረ ማለት ነው ይህም የተባለበት ምክንያት በዓለም ውስጥ እሚገኙት ፍጥረታት መፈጠር የተጀመረባት ስለሆነ ነው ዕለቱም ማክሰኞ(ሠሉስ) ነው፡፡
- **ጥንተ ያን /ዮን/** ፡-ጸሀይ ጨረቃና ከዋክብት የተፈጠሩባት ረቡዕ በመባል ይጠራል ትርጉሙም ጥንተ ብርሀን ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው በመጋቢት 29 በዕለተእሁድ በዘመነ ዩሐንስ ነው፡፡በዘመነ ዩሐንስ መሆኑ እንዴት ይታወቃል ቢሉ በዘመነ ብሉይ የወንጌላውያን ስም የሚታወቅ ሆኖ ሳይሆን የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት አባቶች ዘመናቱን እያካፈሉ ወደ ኋላ በመውሰድ ያገኙት ነው፡፡

ከዛ የዘመን ጥንትነት በመነሳት እስከዛሬ ያለው ወደፊት የሚመጣው በማስላት በዓላት አጽዋማት የሌሊቱ ያደረበትን ጨረቃ የምትወለድበት እና ሌሎች ቀመሮች መስራት ተችሏል፡፡ ይህ የዘመን አቆጣጠር ትምህርት ብዙዎቹ ጥንትነቱን ቢመሰክሩም ጠብቃና ጠንቅቃ የያዘችው ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ናት መሰረቷም ጥንቱ ነውና እንዴት ቢባል ከፍጥረተ ዓለም የሚጀምር ነውና፡፡

- **ሰንበተ ክርስቲያን (እሁድ)** ፡- ለጥንተ ዕለት 1ኛ ለጥንተ ቀመር 6ኛ ለጥንተ ዮን 5ኛ
- **ሰኑይ(ሰኞ)** ፡- ለጥንተ ዕለት 2ኛ ለጥንተ ቀመር 7ኛ ለጥንተ ዮን 6ኛ
- **ማክሰኞ (ሠሉስ)**፡- ለጥንተ ዕለት 3ኛ ለጥንተ ቀመር 1ኛ ለጥንተ ዮን 7ኛ
- **ረቡዕ**፡- ለጥንተ ዕለት 4ኛ ለጥንተ ቀመር 2ኛ ለጥንተ ዮን 1ኛ
- **ሐሙስ** ፡-ለጥንተ ዕለት 5ኛ ለጥንተ ቀመር 3ኛ ለጥንተ ዮን 2ኛ
- **ዓርብ** ፡- ለጥንተ ዕለት 6ኛ ለጥንተ ቀመር 4ኛ ለጥንተ ዮን 3ኛ
- **ቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ)** ፡-ለጥንተ ዕለት 7ኛ ለጥንተ ቀመር 5ኛ ለጥንተ ዮን 4ኛ

፪.፪. ዓዕዋዳት

ባሕረ-ሐሳብ /የዘመን አቆጣጠር/ የሚሰፈረው የሚለካው ዓዕዋዳት ተመልሰው በሚመጡ ድግግሞሽ እየተመሩ የሚፈጥሩት ቁጥር ዘመንን ይሰፍራሉ።

፪.፪.፩. ዓዕዋዳት የሚባሉት እነማን ናቸው

- አጽዋዳት በቁጥር ሰባት ናቸው እነሱም፡-

ሀ. ዓውደ ዕለት ፡- ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉት ቀናት ሲሆኑ ሁልጊዜ በየሰባት ቀኑ ተመላልሰው ይመጣሉ

ለ. ዓውደ ወርኅ ፡- በጸሃይ ሙሉ ፴ (30) ቀን ሲሆን በጨረቃ ግን አንድ ወር ፳፱ (29) አንድ ወር ፴ (30) ይሆናል።ይህ ወር የሚለውን ይወክላል።

ሐ . ዓውደ ዓመት ፡- በጸሐይ **365 ¼ ፫፻፷፭ (፲፭)** ወይም **15 ኬክሮስ** ሲሆን በጨረቃ **354 (፫፻፶፬)** ይሆናል።

መ. ዓውደ አበቅቴ ፡- በአስራ ዘጠን አመት ዞሮ የሚመጣ ሲሆን በአስራ ዘጠን አመት አንድ ጊዜ አልቦ መጥቅር ወአልቦ አበቅሬ ይሆናል።ይህ ማለት መጥቅና አበቅሬ ዜሮ የሚሆኑበት አመት ነው።ምክንያቱ ደግሞ በ ፲፱ (19)ዓመት አንድ ጊዜ ፀሃይ እና ጨረቃ በተፈጠሩበት ፍኖት ውስጥ በተራክቦ /ተገናኝተው/ የሚያድሩበት ስለሆነ ነው።

ሠ. ዐውደ ፀሐይ ፡- በየ ፳፰ (28) አመቱ ዞሮ የሚመጣ ነው። ፀሐይ በተፈጠረችበት በዕለተ ረቡዕ ና ወንጌላዊው ይገኙበታል ይህ ማለት ፀሐይ የተፈጠረችው ወንጌላዊው ደግሞ ማቴዎስ ነው

፡- በሊቃውንት የባህር-ሃሳብ ቀመር ንዑስ ቀመር በመባል ይጠራል።

ረ. ዐውደ ማህተም ፡- በየ ፸፮ (76) ዓመት መላልሶ ይመጣል።ይህ የሚሆንበት ዋነኛ ምክንይት በሰባ ስድስት አመት አንድ ጊዜ አበቅቴው ፲፰ (18) ይሆናል ወንበር ከዜሮ ያንሳል ወንጌለዊው ዮሐንስ ይሆናል።

፡- ለአበቅቴው ፲፰ (18) መጨረሻው ለወንጌላውያን የመጨረሻ ደግሞ ዮሐንስ ነው።በዚህም የተነሳ ዓውደ ማህተም ተብሏል።

፡- ማህተም ማለት ፍጻሜ /የመጨረሻ/ ማለት ነው።

፡- በሊቃውንት የባህር ሃሳብ ቀመር ማዕከላ ቀመር ተብሎ ይጠራል።

ሰ. ዐውደ ዓብይ ቀመር ፡- በ ፭፻፴፪ (532) ዓመት ተመላልሶ ይመጣል ።በዚህ ወቅት ሶስት ነገሮች በጋራ ይገናኛሉ ይኸውም ዕለቱ ሰኞ የቀመር መጨረሻ ነው።አበቅቴው ፲፰ (18) ወንጌላዊው ዩሀንስ ይሆናሉ።

ምዕራፍ ፫

፫.፩. ወንጌላውያን

ወንጌላውያን ማለት በመንፈስ ቅዱስ አትጊነት/ ገላጭነት / ወንጌል /የምስራች ቃሉ/ የጻፉት ቅዱሳን ሰዎች ናቸው፡፡

፫.፩.፩ . ወንጌላውያን ቁጥራቸውና ትርጓሜው

- ወንጌላውያን ቁጠራቸው አራት(4) ሲሆኑ ሁለቱ ከሐዋሪያት ማቴዎስና ዩሀንስ ሁለቱ ደግሞ አርድእት ማርቆስና ሉቃስ ናቸው ፡፡
- ማቴዎስ በገጸ ሰብዕ ይመስላል ይህ የሆነበት ምክንያት ምድራዊ ልደት በመዘርዘር በመጀመሩ ነው፡፤ማርቆስ ደግሞ በገጸ አንበሳ ይመስላል በግብጽ ይመለክ የነበረው አንበሳ የክርስቶስ ወንጌል በማስተማር ወደ ማመን ስላመጣቸው ነው ሉቃስ ደግሞ በለህም ይመስላል ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ መድህን ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት በግርግም መወለዱ ስለሚዘረዝር ነው፡፡ዩሀንስ በንስር ይመሰላል ንስር ከሰማይ ሆኖ የራቀውን አቅርቦ ይመለከታል ዩሀንስም ሰማያው የሆነው የነገረ መለኮት ሚስጥር ተረድቶ በመጻፍ ነው፡፡

፫.፩.፪. ቁጥራቸው አራት መሆኑ ትርጉሙ

በአራት ቁጥር የሚታወቁ በቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡እነሱም በ4ቱ ኪሩቤልና ሱራፌል ፡- እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ናቸው፡፡ የሰው እንስሳና ኪሩቤል ናቸው፡፤አይናቸው የበዛ ንስር እና የአንበሳ ሱራፌል ይባላሉ፡፡ክንፋቸው ስድስት የሆነ ማለት ነው

በ4ቱ ክፍለ ዘመን ጸደይ፣ክረምት፣መጸውእና ሐጋይ(በጋ) ናቸው፡፡

- ጸደይ ወርሃ ዘርዕ ነው በማቴዎስ ይመሰላል ከሁሉ አስፍቶ ወንጌል ጽፏልና
- ክረምት ወርሃ ማይ (ወሃ)ነው፡፡በማርቆስ ይመሰላል ወንጌሉን የሚጀምረው የጥምቀቱ ነገር በመዘርዘር በመሆኑ ነው፡፡
- መጸው ወርሃ ነፋስ በሉቃስ ይመሰላል ነፍስ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል ሉቃስ መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ያድራልበማለት ወንጌሉን ይጀምራል፡፡
- ሐጋይ ወርሃ ዕሳት በዩሀንስ ይመሰላል የሐንስ ወንጌሉ በጣም ጠንካራናረቂቅ የሆነ ወንጌሉ ሲጀምር ገና በረቂቅ አጻጻፍ ይጀምራልና፡፡

➢ በ4ቱ ባህሪያት ፡- ነፋስ ፣ዕሳት፣ውሃ እና መሬት ፍጥረታትን ለመፍጠር ከዚህ እንደማይወጣ ሁሉ ከ4ቱ ወንጌላውያን ትምህርት የሚወጣ የለምና፡፡

➢ በ4ቱ መዓዝነ ዓለም ፡- ሰሜን ፣ደቡብ፣ምስራቅ እና ምዕራብ

➢ በ4ቱ ከዋክብት፡- ምልክኤል፣ ናርኤል፣ምልኤል፣ህልመልሜሌክ

- በ4ቱ አፍላጋት፡- ኤፍራጠስ ፣ጤግሮስ ፣ግዮን፣ኤፌሶን እና ሌሎችም

፫.፩.፫ .ወንጌላውያን በዘመን መጠራታቸው

ሊቃውንት ዘመናቱን በወንጌላውያን ስም የሰየሙት ወንጌላውያን በተለያየ ቦታ ፣ በተለያየ ጊዜ እና በተለያየ ቋንቋ ለሁሉም መሰረት የሆነችወን ደጊቱ ሕገ ወንጌል ስለጻፉ ለውለታቸው ያደረጉት ነው፡፡ቅዱሳን ውለታ ዋሉልኝ ባይሉም እኛ ከእነሱ በኂላ የተነሱ ልጆቻቸው ግን ለፍቅራቸው መግለጫ ይሆን ዘንድ መታሰቢያ ያደርጉላቸዋል፡፡

በዚህም መሰረት ወንጌላውያን ሳይገናኙ የጌታን ቃል ለአራት ተከፋፍለው ስለጻፉት ዘመናትን ከፍለው ሊቃውንት ለመታወቂያቸው አድርገውላቸዋል፡፡

በብሉይ ኪዳን ወንጌላውያን የሉም እንደምን በብሉይ እንጠራቸዋለን ብንል ዘመናትን ለአራት ለአራት እያካፈልን ወደኂላ ስንመለስ ዓለም የተፈጠረበት ዘመን ዮሐንስ መሆኑን እንረዳለን፡፡

፫.፪ . ወንጌላውያን እንዴት ይገኛሉ?

ወንጌላውያንን ለማግኘት መጀመሪያ ዓመተ ዓለምን ማግኘት ይኖርብናል፡፡ዓመተ ዓለም ማለት የዓመተ ምህረት ና የዓመተ ኩነኔ ድምር ውጤት ነው፡፡

ዓመተ ዓለም = ዓመተ ምህረት ተ ዓመተ ኩነኔ(ፍዳ)

ምሳሌ .፩. የ2001 ዓ.ም ብንመለከት፡፡

ዓመተ ዓለም = 1146 + 5500

= 6646

ዓመተ ዓለም ከተገኘ ወንጌላዊውን /ዘመኑ ማን እንደሆነ/ ለማወቅ እንችላለን፡፡ስለዚህም

$$\text{ወንጌላዊ} = \frac{\text{ዓመተ ዓለም}}{4}$$

ምሳሌ. ፪. የ2001ዓመተ ምህረት እንስራ ?

$$\text{ወንጌላዊ} = \frac{6646}{4} = 187$$ ጊዜ ደርሶ 1 ይቀራል፡፡

- ከተሰራው የሂሳብ ቀመር የሚተርፈው . አንድ ከሆነ ዘመኑ ማቴዎስ
  . ሁለት ከሆነ ዘመኑ ማርቆስ
  . ሦስት ከሆነ ዘመኑ ሉቃስ
  . ያለምንም ቀሪ የተካፈለ ከሆነ ዘመኑ ዮሐንስ ይሆናል

❖ ስለዚህም የ1146 ዓመተ ዘመኑ ማቴዎስ ይሆናል።

፫.፫. መባቻ (መጠነ- ሳብዒት)

- መባቻ ማለት መጀመሪያ ወይም መግቢያ ማለት ነው ።መባቻ ወንጌላዊው ወይም መስከረም አንድ ምን ዕለት እንደሚውል ለማወቅ የምንችልበት መንገድ (ቀመር) ማለት ነው፡፤

$$\text{መባቻ} = \frac{\text{ዓመተ ዓለም} + \text{መጠነ ራቢዒት}}{7}$$

መጠነ ራቢዒት፡- ማለት በዘመን ውስጥ የሚደርሰው አንድ እጅ ማለት ነው።
ወንጌላውያን ለማግኘት ዓመተ ዓለም ለ4ት ስናካፍለው የደረሰው አንድ አራተኛ(¼) ማለት ነው።

ምሳሌ ፩. 2001 ዓ.ም መጠነ ራቢዒት 1875 በዚህ ተመስርተን መባቻውን እንስራ

$$\text{መባቻ} = \frac{\text{ዓመተ ዓለም} + \text{መጠነ ራቢዒት}}{7} = \frac{7501 + 1875}{7} = \frac{9376}{7} = 1339$$ ጊዜ ደርሶ 3ይቀራል።

ለሰባት ገድፈን የሚተርፈው ፡- **አንድ ከቀረ ማክሰኞ**
ሁለት ከቀረ ረቡዕ
ሶስት ከቀረ ሐሙስ
አራት ከቀረ አርብ
አምስት ከቀረ ቅዳሜ
ስድስት ከቀረ እሁድ
ምንም ካልቀረ ሰኞ

ስለዚህ የ2001 ዓ.ም መባቻ 3 ስለሆነ **ሐሙስ ዕለት** ነው የዋለው ማለት ነው።

መልመጃ . ፪

➢ **ተማሪዎች 1994 ዓ.ም መባቻ ምን ቀን እንደሆነ አስልታችሁ አግኙ?**

ምዕራፍ ፬

ወንበር

፩.፮. ወንበር በንዑስ ቀመር (በዘመናዊ)

- ወንበር መአበቅሬት ና መጥቅር አደላድሎ ለማውጣት ሚጠቅም ማለት ነው፡፡ወንበር በተለያ መንገዶች በመጠቀም ማግኘት እንችላለን በዚህ ክፈል ግን በዘመናዊ አሰራር ያለው መንገድ እንመለከታልን፡፡

ወንበር = ዓመተ ዓለም / 19

ምሳሌ. ፩ . የ2001 ዓ.ም ብንመለከት

ወንበር = 7501 / 19 = 394 ጊዜ ደርሶ 15 ይቀራል

አዋጅ. ፩. ‹‹ **አሐደ አዕተት ለዘመን**›› አንዱን ለዘመኑ ሰጠው ስለዚህ የ2001 ዓ.ም 15 የቀረን አንዱን ለዘመን ስጥ በሚለው ሕግ መሰረት አንድ ስንሰጥ 14 ይሆናል ማለት ነው፡፡14 የ2001 ዓ.ም ወንበር ይባላል፡፡

መልመጃ . ፫

- **የ1968 ዓ.ም ወንበር ስንት እንደሆነ ሰርታችሁ አሳዩ ?**

፩.፪. ወንበር በአበው ሊቃውንት ቀመር

ሊቃውንት ወንበርን ለማግኘት በቅድሚያ ከጌታችን ልደት በፊት ያለውን ዘመን እና ከገታ ልደት በኋላ ያለውን ዘመን በመደመር ዓመተ ዓለምን በማግኘት ያሰሉታል፡፡አበው ሊቃውንት ወንበርን ለማግኘት ሦስት ቀመር ይጠቀማሉ፡፡እነሱም ፡-

ሀ. ንዑስ ቀመር ፡- ብዛቱ (፫) 3 ነው፡፡

ዘመኑ (፲፱)19 ነው፡፡

ለ.ማዕከላይ ቀመር ፡- ብዛቱ (፮) 6 ነው፡፡

ዘመኑ (፸፮) 76 ነው፡፡

ሐ. ዓቢይ ቀመር ፡- ብዛቱ (፲፭) 15 ነው፡፡

ዘመኑ (፭፻፴፪) 532 ነው፡፡

በእነዚህ ሶስት ቀመሮች በመተቀም የየዘመኑን ወንበር ማግኘት ይችላሉ፡፡

ምሳሌ .፭. የ2001 ዓ.ም እንሰራለን

በመጀመያ አመት ዓለም እንሰራለን ዓመተ ዓለም = ዓመተ ምህረት + ዓመተ ዓለም

= 2001 + 5500

= 7501

- 7000/ 532 ሲገደፍ 13 ጊዜ ደርሶ 84 ይቀራል፡፡ 501 + 84 / 532 አንድ ጊዜ ደርሶ 52 ይተርፋል 52/ 19 ሲገደፍ 2 ጊዜ ደርሶ 15 ይቀራል፡፡ ስለዚህም አንድ ለዘመን ስጥ በሚለው ህግ መሰረት አንድ ስንሰጥ የ2001 ዓ.ም ወንበር 14 ይሆናል ፡፡

መልመጃ . ፬

> **የ1986 ዓ.ም ወንበር በአበው ቀመር ስንት እንደሆነ ሰርታችሁ አሳዩ ?**

የሶስቱ ቀመር የብዜት ሕርግራግ

ብዜት	ንዑስ ቀመር	ማዕከላይ ቀመር	ዓቢይ ቀመር
1	19	76	532
2	38	152	1064
3	57	228	1596
4	76	304	2128
5		380	2660
6		456	3192
7		532	3724
8			4256
9			4788
10			5320
11			5852
12			6384
13			6916
14			7448
15			7980

ምዕራፍ ፭

፭.፩. አበቅቴ

፭.፩.፩. አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው

- ❖ አፖክቴ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ተረፈ ዘመን ማለት ነው፡፡ ወላዲ አበቅቴ (ጥንተ አበቅቴ) የሚባለው 11 ነው፡፡
- ❖ ፲፩ (11) ቁጥር ፦ በሱባዔ የተገኘ ነው አንድም በጸሐይ እና በጨረቃ መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡

፭.፩.፪. አበቅቴ ለምን ይጠቅማል

- ሌሊት ያስገኛል
- ጨረቃን ያስገኝልኛል
- ጸሎት ለማስረቂያ ለማውጫ እንገለገልበታለን፡፡

፭.፩.፫ .አበቅቴን የማግኛ ሁለት መንገዶች

፩ኛ. መንገድ

የዘመኑ አበቅቴ = ወንበር x ጥንተ አበቅቴ / 30

$$\text{የዘመኑ አበቅቴ} = \frac{\text{ወንበር} \times \text{ጥንተ አበቅቴ}}{30}$$

ምሳሌ ፩ ፦ 2002 እንስራ

$$\text{የዘመኑ አበቅቴ} = \frac{15 \times 11}{30} = \frac{165}{30} =$$ 5 ጊዜ ደርሶ 15 ይቀራል ይህ የ2002 አበቅቴ ነው

፪ኛ መንገድ

የዘመኑን አበቅቴ =ያለፈው አበቅቴ + ወላዲ አበቅቴ

ምሳሌ .፪ ፦ የ2002 ዓ.ም አበቅቴ ስላገኘን የ2003ዓ.ም አበቅቴ እንስራ

የ2003ዓ.ም አበቅቴ = የ2002ዓ.ም አበቅቴ + ወላዲ አበቅቴ

= 15 +11 = 26

ስለዚህም የዘመኑን አበቅቴ ካገኘን በኃላ ጨረቃ እና ሊሊት እንዴት እንደምናገኝ ለማየት እንሞክራልን፡፡

መልመጃ . ፭

- ➢ የ2011 ዓ.ም አበቅቴ በሁለቱም መንገድ ስርታችሁ አሳዩ ?

- **ሌሊት**

ሌሊት = ዕለት + ሕጸጽ + አበቅቴ

ምሳሌ ፷. የካቲት 1. 2002 ዓ.ም እንስራ

ሌሊት= 1 + 3 + 15= 19

መልመጃ . ፮

➢ የ2002 ዓ.ም ጥቅምት 16 ሌሊቱን ሰርታችሁ አሳዩ ?

- **ጨረቃ**

ጨረቃ= ዕለት +ሕጸጽ+ አበቅቴ + የጨረቃ ተውሳክ

ወይም

ጨረቃ = የጨረቃ +ተውሳክ (4)

ምሳሌ. ፱ . የካቲት 1 2002 ዓ.ም ጨረቃ እንስራ

ዕለት(መዓልት) + ሕጸጽ + አበቅቴ + የጨረቃ ተውሳክ

1 + 3 + 15+ 4= 23

መልመጃ . ፯

➢ የ2002 ዓ.ም ጥቅምት 16 ጨረቃ ሰርታችሁ አሳዩ ?

ሕጸጽ፡- ማለት ሐጸ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ጎደለ ማለት ነው ሕጸጽ ማለት ደግሞ ጉድለት ማለት ነው፡፡ ይህ የተገኘው ደግሞ ጸሐይ በወር ሙሉ ሰላሳ ቀን ስትሆን ጨረቃ ግን በአንድ ወር 29 በአንድ ወር 30 ትዞራለች፡፡ ስለዚህም በሁለት ወር የምትጎድለው ሲደመር <u>**በዓመት ስድስት ሕጸጽ**</u> ይሆናል፡፡

፩.፪. መጥቅዕ

- መጥቅዕ ማለት ጸዋዒ አስተጋባዒ ወይም ደወል ማለት ነው ደወል በተመታ ጊዜ የራቁት ይቀርባሉ የተበተኑት ይሰበሰባሉ እኒዲሁም መጥቅዕ በዓላትን እ አጽዋማትን ይሰበስብልናል፡፧
- ስለዚህም መጥቅዕ ማለት በዓላት እና አጽዋማትን የሚያስገኝ ማለት ነው።
- ወላዲ (ጥንተ) መጥቅዕ መጠኑ 19 ነው።

፩.፪.፩ . መጥቅዕን የማግኛ ሁለት መንገዶች

1ኛ መንገድ

$$\text{የዘመኑ መጥቅዕ} = \frac{\text{ወንበር x ጥንተ(ወላዲ) መጥቅዕ}}{30}$$

ምሳሌ. ፲. 2002 ዓ.ም የዘመኑ መጥቅዕ $\frac{15 \times 19}{30} = \frac{285}{30}$ = ዘጠኝ ጊዜ ደርሶ 15 ይቀራል።

መልመጃ . ፰

- የ2011 ዓ.ም አበቅቴ ሰርታችሁ አሳዩ ?

2ኛ መንገድ

የዘመኑ መጥቅዕ = ያለፈው መጥቅዕ+ ወላዲ መጥቅዕ

ምሳሌ ፲፩. የ2003ዓ.ም መጥቅዕ = የ2002ዓ.ም መጥቅዕ + ወላዲ መጥቅዕ

= 15 +19 = 34 በ30 ስንገድፈው 4 ይቀራል ይህም መጥቅዕ ነው።

መልመጃ . ፱

- **የ2011 ዓ.ም አበቅቴ ሰርታችሁ አሳዩ ?**

- **ማስታወሻ ፡- አበቅቴ እና መጥቅዕ ሲደመር ከ ፴ (30) አይበልጡም ከ ፴ (30)ም አያንሱም**

፩.፫.ተውሳክ

ወሰከ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ጨመረ ማለት ነው። ተውሳክ ጭማሪ ማለት ነው እያንዳንዱ ቀናት እና አጽዋማት የራሳቸው የሆነ ተውሳክ (ጭማሪ) አላቸው።

- ሁለት ዓይነት ተውሳክ አሉ **ሀ. የዕለት ተውሳክ**
  ለ.የአጽዋማት ተውሳክ

ሀ. የዕለታት ተውሳክ

- <u>የዕለት ተውሳክ እንዴት (ከየት) ተገኘ</u>

1.ከበዓለ መጥቅዕ ሳኒታ ጾመ ነነዌ እስከ ዋለበት ያሉት ቀናት ተቆጥሮ ለሰላሳ ስንገድፈው ይገኛል።

ዕለት	ከበዓለ መጥቅዕ በኃላ ቀናት	የተገኘው ጭማሪ (ተውሳክ)
ቅዳሜ	128/30	8
እሁድ	127/30	7
ሰኞ	126/30	6
ማክሰኞ	125/30	5
ረቡዕ	124/30	4
ሐሙስ	123/30	3
ዓርብ	122/30	2

2. <u>ከአይጋረ(እግሮች) ጸሐይ</u>

❖ የአይጋረ ጸሐይ መጠኑ 2100 ነው። የሰባቱን ዕለታት ተውሳክ ብንደምረው 35 ይመጣል ይህን በ60 ብናበዛው 2100 ይሆናል ወይም የአይጋረ ጸሐይ መጠን ለስድሳ ብንገድፈው የዕለት ተውሳክን ያስገኝልናል።

ለ.የአጽዋማት ተውሳክ

- <u>የአጽዋማት ተውሳክ እንዴት (ከየት) ተገኘ</u>

1. ከጾመ ነነዌ ሳኒታ እስከ በዓላት እና አጽዋማት ያሉት ቀናት በማስላት ይገኛል

በዓለት እና አጽዋማት	ከጾመ ነነዌ እስከ በዓላት እና አጽዋማት ያሉት የቀናት ብዛት	ተውሳክ
ዓቢይ ጾም	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ዓቢይ ጾም ያሉት ቀናት	14
ደብረ ዘይት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ደብረ ዘይት በዓል ያሉት ቀናት 41/30	11
ሆሳህና	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ሆሳህና በዓል ያሉት ቀናት 62/30	2
ስቅለት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ስቅለት በዓል ያሉት ቀናት 67/30	7
ትንሳኤ	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ትንሳኤ በዓል ያሉት ቀናት 69/30	9
ርክበ ካህናት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ርክበ ካህናት በዓል ያሉት ቀናት 93/30	3
ዕርገት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ዕርገት በዓል ያሉት ቀናት 108/30	18
ጰራቅሊጦስ	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ጰራቅሊጦስ በዓል ያሉት ቀናት 118/30	28
ጾመ ሐዋርያት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ጾመ ሐዋርያት ያሉት ቀናት 119/30	29
ጾመ ድኅነት	ከጾመ ነነዌ ሳኒታ(ማግስት)እስከ ጾመ ድኅነት ያሉት ቀናት 121/30	1

2. <u>ከአውታረ ጸሐይ</u>

- የአውታረ ጸሐይ መጠኑ 7320 ነው። የአጽዋማት እና በዓላት ተውሳክ ብንደምረው 122 ይመጣል ይህን በ60 ብናበዛው 7320 ይሆናል።

ምዕራፍ ፯

፯.፩. መባጃ ሐመር

- መባጃ ሐመር ከሁለት ጥምር ቃል የተገኘ ሲሆን እነዚህም መባጃ እና ሐመር ናቸው።
  መባጃ ማለት ባጀ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን መባጃ መክረሚያ ማለትነው
  ሐመር ማለት ደግሞ መርከብ ማለት ነው
- በዓመት ውስጥ ያሉትን በዓለትን እና አጽዋማት የሚያስገኝልን ስለሆነ መባጃ ሐመር መክረሚያ መንቀሳቀሻ ይባላል።

መባጃ ሐመርን ለማግኘት

መባጃ ሐመር =መጥቅዕ + የዕለት ተውሳክ

አዋጅ ፩. መጥቅዕ ከ14 በላይ ከሆነ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ይውላል።

አዋጅ ፪. መጥቅዕ ከ14 በታች ከሆነ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ይውላል።

አዋጅ ፫. በዓለ መጥቅዕ መስከረም ከዋለ ጾመ ነነዌ ጥር ትውላለች።

አዋጅ ፬. በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ከዋለ ጾመ ነነዌ የካቲት ትውላለች።

አዋጅ ፭. መጥቅዕ እና የዕለት ተውሳክ ሲደመር ከሰላሳ በላይ ከተገኘ ጾመ ነነዌ የካቲት ትውላለች።

አዋጅ ፮. ወንበር አልቦ ሲመጣ መስከረም 30 የዋለበት የዕለት ተውሳክ መባጃ ሐመር ይሆናል።

አዋጅ.፯. ወንበር አልቦ በሚሆንበት ዘመን ሁልጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት ትውላለች።

ምሳሌ ፲፩ . የ1996 ዓ.ም እንመልከት

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + የዕለት ተውሳክ

= 21+ 3 =24 (ነነዌ ጥር 24 ትውላለች።)

- **ዓቢይ ጾም=** መባጃ ሐመር + ዓቢይ ጾም ተውሳክ

  =4 + 14= 38/30=የካቲት 8
- **ደብረ ዘይት=** መባጃ ሐመር + የደብረ ዘይትተውሳክ

  =24 + 11= 35/30 መጋቢት 5
- **በዓለ ሆሳዕና =** መባጃ ሐመር + የሆሳዕና ተውሳክ

  =24 + 2= መጋቢት 26

- **በዓለ ስቅለት = *መባጃ ሐመር+ የበዓለ ስቅለት***

  = 24+ 7= 31/30 *ሚያዚያ* 1

- **በዓለ ትንሳኤ** =*መባጃ ሐመር+ የበዓለ ትንሳኤ ተውሳክ*

  = 24 +9 =33/30 *ሚያዚያ* 3

- **በዓለ ርክበ ካህናት=*መባጃ ሐመር+ የበዓለ ርክበ ካህናት ተውሳክ***

  =24 +3= 27 *ግንቦት* 27

- **በዓለ ዕርገት = *መባጃ ሐመር+ የበዓለ ዕርገት ተውሳክ***

  =24 +18=42/30 ሰኔ 12

- **በዓለ ጰራቅሊጦስ** =*መባጃ ሐመር+ የበዓለ ዕርገት ተውሳክ*

  = 24 +28 =52/30 ሰኔ 22

- ***ጾመ ሐዋርያት***=*መባጃ ሐመር+ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ*

  =24+ 29= 53/30 ሰኔ 23

- ***ጾመ ድኅነት*** = *መባጃ ሐመር+ የጾመ ድኅነት ተውሳክ*

  = 24 +1 =25 ሰኔ 25

መልመጃ .፲

> ➢ የ2004 ዓ.ም በዓላት እና አጽዋማት ሰርታችሁ አሳዩ ?

የበዓላት እና የአጽዋማት ኢይዓርግ እና ኢይወርድ

አጽዋማት እና በዓላት	ኢይወርድ	ኢይዓርግ
ጾመ ነነዌ	ጥር 17	የካቲት 21
ዓቢይ ጾም	የካቲት 1	መጋቢት 5
ደብረ ዘይት	የካቲት28	ሚያዚያ 2
ሆሳህና	መጋቢት 19	ሚያዚያ 23
ስቅለት	መጋቢት 24	ሚያዚያ 28
ትንሳኤ	መጋቢት26	ሚያዚያ 30
ርክበ ካህናት	ሚያዚያ 20	ግንቦት 24
ዕርገት	ግንቦት 05	ሰኔ 9
ጰራቅሊጦስ	ግንቦት 15	ሰኔ 19

ጾመ ሐዋርያት	ግንቦት 16	ሰኔ 20
ጾመ ድኅነት	ግንቦት 18	ሰኔ 22

❖ የጠፋብንን (በዓለ መጥቅዕን) ለማግኘት

የጠፋብን ዕለት = ጥንተዮን + አጽፈ ወርኀ + ዕለት (መዓልት)

ለምሳሌ ፲፫ ፡- ጥር 22/2009 ዓ.ም መቼ እንደዋለ እንስራ

የጠፋብን ዕለት = ጥንተዮን + አጽፈ ወርኀ + ዕለት (መዓልት)

5 +10 + 22 = 37 ሲገደፍ በ7 አምስት ጊዜ ደርሶ 2 ይተርፋል፡፡

የተገኘውን ውጤት በጥንተ ዕለት

- ስለሆነም አንድ ከመጣ እሁድ ሁለት ከሆነ ሰኞ 3 ማክሰኞ 4 ረቡዕ 5 ሐሙስ 6 አርብ አልቦ ከሆነ ቅዳሜ ይሆናል፡፡
- ሰለዚህም ጥር 22 /2009 ዓ.ም የዋለው ዕለት ሰኞ ይሆናል፡፡

ያለተውሳክ በቋሚነት በዓመት ውስጥ የሚመላለሱ አጽዋማት እና በዓላት

- **መስቀል** ፡- መስከረም 17 እና መጋቢት 10 የሚታሰብ ይሆናል
- **ጾመ ነቢያት**፡- ከኅዳር 15 እስከ ታህሳስ 28 የሚጾም ሲሆን በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ጳጉሜን ስድስት ስትሆን ኅዳር 14 ጀምሮ ታህሳስ 27 የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡
- **በዓለ ልደት**፡- የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከእናታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ ሰው መሆኑን የምናከብርበት ነው፡፡
- **ግዝረት** ፡- ጥር 6 ይታሰብበታል፡፡
- **ጾመ ገሐድ**፡- ይህ ጾም የጥምቀት ዋዜማ ጥር10 የሚጾም ስሆን ምክንያቱ ደግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል መከበር ያለበት በፍስሐ ሐሴት በመሆኑ ረቡዕ እና አርብ የሚሉትን ቀድሞ ለመጾም ነው ነገር ግን አባቶች ረቡዕ እና አርብ እየጠበቁ መጾም ስለሚያዘናጋ ሁልጊዜ የጥምቀት ዋዜማ እንዲንጾም አዘዋል፡፡
- **በዓለ ጥምቀት**፡- ሁልጊዜ ጥር 11 የሚከበር በዓል ነው ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባህረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ በሰላሳ ዘመኑ የእዳ ደብዳቤያችን ሊያጠፋ ለእኛ አርአያ ለመሆን የተጠመቀበት የሥላሴ አንድነት እና ሶስትነት የተገለጸበት በዓል ነው፡፡
- **በዓለ ስምዖን** ፡- የካቲት 8 ቀን ይታሰባል የኦሪትን ስርዓት ለመፈጸም ወደ ምኩራብ የሄደበት በዓል ነው፡፡
- **በዓለ ብስራት** ፡- ጥንተ ዕለቱ መጋቢት 29 ሲሆን የጾም ወቅት ስለሆነ በዓሉ ታህሳስ 22 ይከበራል፡፡
- **በዓለ ቶማስ (ዳግም ትንሳኤ**) ፡- በዓለ ትንሳኤ በዋለ ሳምነት እሁድ ይከበራል፡፡
- **ጾመ ፍልሰታ** ፡- ከነሐሴ 1 እስከ 16 ያለው ጊዜ ነው፡፡

- **በዓለ ደብረ ታቦር** ፦ ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን ግርማ መንግስቱን የገለጸበት ነው ነሐሴ 13 ይከበራል።

ምእራፍ ፯

፯.፩. ክፍለ ዓመት (ዘመን) በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት

- በቤተክርስቲያን የሚነበበው መጽሐፍ የሚሰብከው ስብከት የሚዘመረው መዝሙር የሚቀደሰው ቅዳሴ ያሉት ወቅቶች በዓላት እና አጽዋማት የሚመለከት ነው።
- እነዚህም መጸው ሐጋይ(በጋ) ጸደይ (በልግ) እና ክረምት ናቸው።

፩ኛ መጸው፡- ማለት የአበባ ወራት ማለት ነው ይህም ከመስከረም 26 -ታህሳስ 25 ደረስ ያለው ጊዜ ነው።መጸው በውስጡ የራሱ የሆኑ ክፍሎች አሉት እነዚህም፡-

ሀ.ዘመነ ጽጌ ፡- ከመስከረም 26 እስከ ኅዳር 5 ያሉት ቀናት ናቸው።

- የእመቤታችንን ከልጇ ጋር ያደረገችውን ስደት በማሰብ የሚቆይበት ወቅት ነው። አንድም የምድር ዕጽዋት እና አዝዕርት ለፍሬ መብቃት እያሰብን እግዚአብሔርን የማናመሰግንበት ነው አንድም በአበባ የምትመሰለውን ድንግል ማርያምን እናስባበታለን።

ለ.ዘመነ አስተምሕሮ ፡- ማለት ምሕላ ልመና ምልጃ ማለት ነው። ከኅዳር6- ታህሳስ6 ያለው ቀን ነው። እግዚአብሔር ታጋሽ ይቅርባይ የቸርነት ስራ መስራቱን እናስበብበታለን።

ሐ.ጾመ ነቢያት ፡- ከኅዳር 15 - ታህሳስ 28 ነቢያት ና ተወለድ ውረድ ክንድህ ስደድልን እያሉ የጾሙት ጾም ነው። በዚህ ጾም ውስጥ ሶስት ክፍሎች እናያለን።

- **ስብከት**፡- በኦሪት አምላክ ሰው እንደሚሆን መሰበኩ ይታሰብበታልን።
- **ብርሃን**፡- ብርሃን ክርስቶስ ወደ ጨለማው ዓለም መምጣቱን ብርሃን አእንደምናይ ይታሰብበታል።
- **ኖላዊ** ፡- እረኛ ማለት ነው ስለመንጋዎቹ ሕወቱን አሳልፎ የሚሠጥ ቸር እረኛ መሆኑ ይታሰብበታል።

፪ኛ ክፍለ ዘመን ሐጋይ ፡- ደረቅ የደረቅ ወራ ማለት ነው፤ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት25 ያለውን የሚይዝ ይሆናል።

ሀ.ዘመነ ልደት፡- ከታህሳስ 26 እስከ ጥር 9 ክርስቶስን መወለዱን ሰብአሰገል እንደሰገዱለት መላእክት ከእረኞች ጋር እንደዘመሩላት እንሰሳት ትንፋሻቸውን እንደገበሩለት እናስብበታልን።

ለ ዘመነ አስተርእዮ ፡- መገለት መታየት ማለት ነው። ከጥር 11 እስከ ጾመ ነነዌ ያለው ነው። በዚህ ወቅት አምላክ ሰው ሆኖ መገለጡን በዮርዳኖስ መጠመቁን የአንድነት እና የሦስትነት ምስጢር መታወቁን ኢሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተዓምር ማድረጉ ይወሳበታል።

ሐ.ጾመ ነነዌ ፡-የነነዌ ሰዎች ለኃጢያታቸው የገቡትን ንስሐ የእግዚአብሔር መኀሪነት ይታሰብበታል፡፡

መ.ዘመነ መርዓዊ ፡- ከጾመነነዌ እስከ ዓቢይ ጾም ያለው ወቅት ነው፡፡

፫ኛ. ክፍለ ዓመት ጸደይ (በልግ) ፡- ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ያለው ወቅት ነው፡፡ ይህም ክፍለ ዓመት እንደሌሎቹ ሁሉ የተለያዩ ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

ሀ.ዓቢይ ጾም ፡- ከዓቢይ ጾም እስከ ቅዳም ስዑር ያለው ነው፡፡ሰምንታቱ የራሳቸው የሆነ መለያ አላቸው፡፡

- **ዘወረደ** ፡- */ዮሐ 3፡13-25/* ወደዚህ ዓለም ስለምምጣቱ
- **ቅድስት** ፡- */ማቴ6፡16-25/* የሰንበተ ክርስቲያን ቅድስና ይመለከታል፡፡
- **ምኩራብ** ፡- */ዮሐ 2፡12/*-ፍጻሜ በምኩራብ ገብቶ እንዳስተማረ የሚሸጡና የሚለውጡትን እንዳባረረ
- **መጻጉዕ** ፡- */ዮሐ 5፡1-25* /ድውያንን መፈወሱን የሚዘከርበት ክፍል ነው፡፡
- **ደብረዘይት**፡- */ማቴ 24፡1-36/* በደብረዘይት ተራራ ነገረ ምጽዓቱን ማስተማሩ
- **ገብርኄር** ፡- /ማቴ 25፡14-30/ ታማኝ እና በጎ የሆነው ባርያ ወደጌታ ደስታ ግባ የተባለበት
- **ኒቆዲሞስ** ፡- */ዮሐ 3፡1-12 /*ኒቆዲሞስ የአይሁድ መምህር በሌሊት ከጌታ ዘንድ መማሩ ይታሰባል፡፡
- **ሆሳዕና**፡- */ዘካ 9፡9/* ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ እየተመሰገነ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱ ይወሳበታለ፡፡

ለ.ዘመነ ትንሳኤ ፡- ትንሳኤ ከዋለበት እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ ያለው ጊዜ ነው፡፡ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ድል አድርጎ መነሳቱን ነፍሳትን ከሲኦል አውጥቶ ወደ ገነት ማስገባቱን እናስብበታል፡፡በዚህ ክፍል ውስጥ ርክበ ካህናት እና ዕርገት የሚካተት ይሆናል፡፡

ሐ.ዘመነ ጰራቅሊጦስ ፡- መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል መሰጠቱን የምናስብበታለን ይህ ቀን የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ይባላል፡፡

መ.ጾመ ሐዋርያት ፡- ከበዓለ ጰራቅሊጦስ ማግስት እስከ ሐምሌ 5 ያለው ወቅት ነው ሐዋርያት ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት በጾም በጸሎት የጠየቁበት ወቅት ነው፡፡

ሠ.ዘመነ አስተምሕሮ ፡- ከሰኔ 17 ጀምሮ እስከ ሰኔ 25 ያለው ወቅት ነው፡፡

፬ኛ ክፍለ ዓመት ክረምት ፡- ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ቀን ደረስ ያለው ወቅት ነው፡፡

ሀ. ከሰኔ 25 እስከ ሐምሌ 18 ፡- የዝናም የደመና የዘር የቡቃያ ዘመን ተብሎ ይጠራል፡፡

ለ. ከሐምሌ 19 እስከ ነሐሴ9 ፡-የመብረቅ የነጉድጓድ የባህር የወንዞች ወቅት ነው፡፡

ሐ. ከነሐሴ 10 እስከ ነሐሴ 27፡- የፍጥረቱ ሁሉ ዓይን እርሱን ተስፋ ማድረጉን የሚታሰብበት

መ. ከነሐሴ 28 እስከ ጳጉሜን 5(6) ፡-ውጋገን ጽባሕ ጠዋት ብርሃን ይባላል ዳግም ምጽአት የሚታሰብበት

ሠ. ከመስከረም 1 እስከ መስከረም 8 ፡-ዘመነ ዮሐንስ ይባላል፡፡

ረ. ከመስከረም 9 እስከ መስከረም 16 ፡-የተዘራውን ዘር ለፍሬ መብቃቱ ይታሰብበታል፡፡ /ዘመነ ፍሬ/

ሰ. ከመስከረም 17 እስከ መስከረም 25 ፡-የመስቀል ተዐምር

የኢትዮጵያ እና የሌሎች ሀገራት የዘመን አቆጣጠር ልዩነት

- **የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር** ፡- ምንጩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡
  ፡- ዓመቱ 365 ከ6 ሰዓት (ከ15 ኬክሮስ) ነው፡፡
  ፡- የዕለቱ እና የወራቶቹ ስያሜዎች የእግዚአብሔር ስራ ምስክሮች ናቸው፡፡
  ፡- ከጳጉሜን በቀር ሁሉም ወራት ባለ30 ቀን ናቸው፡፡
  ፡- ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ የነበረ አቆጣጠር ነው፡፡
  ፡- የጌታን ልደት የሚቆጥረው ከትንቢተ ነቢያት (ሱባዔ)ተነስቶ ነው፡፡
  ፡- አቆጣጠሩ መሰረት የሚያደርገው ዑደተ ጸሐይ ነው፡፡
  ፡- ባለአራት ወቅቶች ነው፡፡
- **የእስክድርያ የዘመን አቆጣጠር** ፡- ከጥንት ግብጻውያን አቀጣጠር የተወሰደ ነው፡፡
  ፡-የሳምንት ስያሜያቸው የተወሰደው ከአይሁዳውያን ነው፡፡
  ፡-አገልግሎት ላይ የዋለው ሠላሳ ዓመት ልደተ ክርስቶስ አስቀድሞ ነው፡፡
  ፡-ከጳጉሜን በቀር ሁሉም ወራት ባለ30 ቀን ናቸው፡፡
  ፡- መሰረት የሚያደርገው ዑደተ ጸሐይ ነው፡፡
  ፡-ባለ ሶስት ወቅት ክፍል ያለው ነው፡፡
- **የዮልሳውያን የዘመን አቆጣጠር** ፡- ከእስክድርያ አቆጣጠር የተወሰደ ነው፡፡
  ፡- የዕለቱ እና የወራቶቹ ስያሜዎች ከጣዖት አምላካቸው እና
  በነገስታቱ ስም የተሰየሙ ናቸው፡፡
  ፡- ዓመቱ 365 ከ6 ሰዓት (ከ15 ኬክሮስ) ነው፡፡
  ፡- የዓመቱ መጀመርያ ማርች (በእኛ መጋቢት) ነው፡፡
  ፡- ወራቱ የተለያዩ የቁጥር መጠን ነው የያዙት
- **የጎርጎርዮስውያን የዘመን አቆጣጠር** ፡-ከዮልሳውያን አቆጣጠር የተወሰደ ነው፡፡
  ፡-ዓመቱ 365 ከ5 ሰዓት ከ48ደቂቃ ከ46 ሰከንድ ነው፡፡
  ፡- የዓመቱ መጀመርያ ወር ጃንወሪ (በእኛ ታህሳስ) ነው፡፡
  ፡- አቆጣጠሩ የጀመረው በራሳቸው አቆጣጠር 1582 በኃላ ነው፡፡
- **የዓረቦች የዘመን አቆጣጠር** ፡- ምንጩ የጥንቱ ሜሶፖታሚያ አቆጣጠር ነው፡፡
  ፡- የዘመን መነሻቸው የመሐመድ ሂጅራ ነው፡፡
  ፡- ዓመቱ 354 የቀናት ብዛት አለው፡፡

፡- አቆጣጠሩ መሰረት የሚያደርገው ዑደተ ጨረቃን ነው፡፡

እነዚህ በመጠኑ ለማየት ሞክረናል እንጂ በዓለማችን ላይ የተለያዩ የዘመን አቆጣጠር እንዳለ ይታወቃል በልዩነት የጎርጎሮሳውያን እና የእኛን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ለማየት እንሞክራለን፡፡

የጎርጎሮሳውያን እና የእኛን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት

- በብዙ መልኩ ከእኛ የዘመን አቆጣጠር ጋር ልዩነት እንዳለ በቀደመን ክፍል ተመልክተናል ነገር ግን በዝርዝር ማየት እና እውነቱ መመዘን ይገባል ስለሆነም የእኛ እና የጎርጎሮሳውያን የዘመን ቁጥር ልዩነት ከስር መሰረቱ እንመለከታለን፡፡

መሰረታዊ ልዩነቶች ፡-

- **የዕለታት እና ወራት ስያሜ ልዩነት**
- **የአዲስ ዓመት (የዘመን መለወጫ) ልዩነት**
- **የሰባት ዓመት ከስምንት ወር ልዩነት**
- **የ10 ቀናት ልዩነት**

የዕለታት እና ወራት ስያሜ ልዩነት

የዕለታት ስያሜ ልዩነት

ስያሜ	የቃሉ ትርጉም	የተሰየመበት ምክንያት	ስያሜ	የቃሉ ትርጉም (ምንጭ)	የተሰየመበት ምክንያት
እሁድ	አሐደ አንድ አደረገ	ለፍጥረት የመጀመሪያ ቀን ስለሆነ	**SUNDAY**	የጸሐይ ቀን	በጸሐይ ያመልኩ ስለነበር
ሰኑይ (ሰኞ)	ሁለት አደረገ	ለፍጥረት ሁለተኛ ቀን ስለሆነ	**MONDAY**	የጨረቃ ቀን	በጸሐይ ያመልኩ ስለነበር
ሠሉስ (ማግሰኞ)	ሦስት አደረገ	ለፍጥረት ሦስተኛ ቀን ስለሆነ	**TUESDAY**	ቲዩ የሚባል የጦርነት አምላክ	ለእርሱ መታሰቢያ
ረቡዕ	አራት አደረገ	ለፍጥረት አራተኛ ቀን ስለሆነ	**WENEDSDAY**	ታላቁ ዎደን የሚሉት አምለክ አላቸው	ለእርሱ መታሰቢያ
ሐሙስ	አምስት አደረገ	ለፍጥረት አምስተኛ ቀን ስለሆነ	**THURSDAY**	ቶር በሚሉት የነጎድጓድ አምላክ	ለእርሱ መታሰቢያ
አርብ	ማካተቻ	ፍጥረትን ፈጥሮ ያጠናቀቀበት ስለሆነ	**FRIDAY**	የዎደን ሚስት በሆነችው ፍሪግስ ስም	ለእርሷ መታሰቢያ
		ከሰንበት ክርስቲያ			በእርሱ ያመልኩ

ቅዳሜ	ቀዳሚት	ቀድማ የምትመጣ	SATURDAY	ሳተርን በሚባለው ኮከብ	ስለነበር

የወራት ስያሜ ልዩነት

የወራቱ ስያሜ	የቃሉ ፍቺ	የተሰየመበት ምክንያት	የወራቱ ስያሜ	የቃሉ ፍቺ (ምንጭ)	የተሰየመበት ምክንያት
መስከረም	ከረመ		Septembere	ሴፕቴም በግሪክ ሰባት ማለትነው	የጁሊያን አቆጣጠር በመከተል
ጥቅምት	ጠቀመ		October	ኦክቶ ስምንት በላቲን ቋንቋ	››
ኅዳር	አደረ		November	ኖቨም ዘጠኝ	››
ታህሳስ	ፈለገ		December	ዴሴም አስር	››
ጥር	መጠቀ		Januray	ጃኑስ የሚባል ጣዖት	››
የካቲት	ሰበሰበ	የምርት መሰብሰቢያ ስለሆነ	Feburary	መዘጋጀት	በጁላይ አቆጣጠር የአዲስ ዘመን መዘጋጃ ስለሆነ
መጋቢት	መገበ		March	ማርቲቨ የማርስ ጌታ	የጦርነት አምላካቸው ነው ለእርሱ መታሰቢያ
ሚያዚያ	ተኀዳኘ		April	አፍሮዳይት የፍቅር አምላካቸው	ለእርሷ መታሰቢያ
ግንቦት	ገነባ		May	ማርያ በምትባለው አምላካቸው	ለእርሷ መታሰቢያ
ሰኔ	አማረ		June	ጁኖ በምትባለው የጋብቻ ጣዖታቸው	ጥሩ የጋብቻ ወቅት ብላው ያምናሉ
ሐምሌ	ለመለመ		July	በጁሊየስ ቄሣር ስም	ከጎርጎሮሰዊው አቆጣጠር በፊት በጁላይ አቆጣጠር ስለተጠቀሙ ለመታሰቢያ
ነሐሴ	ሠራ		Augest	አውግስጦስ (ቄሳር)	በእኛ አጼ እንደማለት ነው
ጳጉሜን	ጭማሪ				

❖ የርዕሰ አውደዓመት (የዘመን መለወጫ) ልዩነት

- እኛ ኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት በመስከረም የምናከብርበት ምክንያት፡-
  - ጸሐይ የ365 ቀን ጉዞዋን ጨርሳ (ፈጽማ) አዲስ ጉዞዋን የምትጀምረው በዚህ ወር ስለሆነ፡፡
  - ሌሊቱ እና መዓልቱ እኩል 12 ሰዓት የሚሆንበት ስለሆነ
  - ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውኃ በኃላ ጽጌ ያበቀለበት አዲስ ዓመት እንዲያከበር የታዘዘበት ወቅት ስለሆነ /ዝፍ 8፤8 / ኩፋ 7፤24 /
  - ለሙሴ ዘመን መለወጫ እንዲያረው ታዟል፡ ፡ / ዘሌ 23 ፤35 /
  - ንግስተ ሳባ የሰሎሞንን አድንቃ የመጣችበት ወቅት የአዲስ ዘመን መለወጫ ስለነበር
  - የጨለማው ጊዜ የክረምቱ ወራት አብቅቶ የብራው (የብርሃኑ) ወቅት የሚጀምርበት ነው፡፡
- ጎርጎሮሳውያን አዲስ ዓመት በታኅሳስ የሚያከብሩበት ምክንያት እነርሱ እንደሚሉት አዲስ ዓመታችንን በዚህ ወቅት የምናከብረው የጌታችንን የኢየሱስ ልደት መሰረት በማድረግ ነው ይላሉ ነገር ግን በላይኛው ክፍል እንዳየነው ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ነው የዕለታት እና የወራት ስያሜያቸውን በጣዖት ስም እየሰየሙ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ላይ የኑፋቄን ትምህረት እያስተማሩ የምናከብረው የጌታን ልደት ተመርኩዘን ነው ማለት የቋጥኝ ያህል የገዘፈን እውነታን በጠጠር ለመሸፈን መሞከር ይሆንባቸዋል፡፡
- እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ኦርቶዶክሳውያን የዘመን አቆጣጠራች መሰረት የምናደርገው መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ በዚህ ወቅት ለምን እንደምናከበር አንድ ሁለት እያልን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ማቅረብ ችለናል ስለሆነም በሚዛናዊነት እውነቱን መመዘን መረዳት ይቻላል፡፡

❖ የሰባት ዓመት ከስምንት ወር ልዩነት

- ዮልያስ የሚባለው ቄሳር 304 የነበረውን የቀናት ብዛት የነበረውን 355 አደረገው ከዚያ በመቀጠል ዲዮናስዮስ ኤክሲጅየስ የተበላው ደግሞ የሮም ምስረታ ላይ በመመርኮዝ ሲያሰላ በጌታ ልደት ላይ 8 ዓመት ጨመረ (5508ዓ.ም) በማለት በዚህም የሰባት ዓመት ከስምንት ወር ልዩነት ተከሰተ፡፡

❖ የአስር ቀናት ልዩነት

- ግርጎሪ የሚባለው 13ኛው የሮም ፓፓ አንድ ዓመት በውስጡ 365 ቀናት ከ6 ሰዓት የነበረው 365 ከ5 ሰዓት ነው በማለት ወደኃላ የነበረውን በማስላት የ10ቀናት ልዩነት ተፈጠረ፡፡
- በዚህ ሁሉ የታሪክ ሂደት ውስጥ የምንረዳው ሀገራችን ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የነበራት ይዛ የቆየች አሁን ሊላዊነት የሚባል መረብ ወደ አንድ ወረብ በሚስብበት ዘመን የራሷን ይዛ ያለች

ቀዳሚ ምድር ናት ስለሆነው ሁላች ይህ መለያ የቤተክርስቲያን ትምህርት ጠብቀን ለመጪው ልናስረክብ ይገባናል፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

- በአብዛኛው ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የወንበር ቀለም ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡
- ወንጌል ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ 1959 ዓ.ም
- መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ እና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት 1980 ዓ.ም
- ባህረ ሐሳብ የቀመር እና የሥነ ፈለክ ምሥጢር በአለቃ ያሬድፈንታ ወልደ ዮሐንስ 2004 ዓ.ም
- መጽሐፈ ስንክሳር ከመስከረም- የካቲት
- መዝሙረ ዳዊት ንባብ ከነትርጓሜው
-

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር
አሜን